# ቁጭ በሉ መንግስት

ከወጨፎ ኖርዌይ

አራዶች ከተማችን ውስጥ ስለውስልትና የሚቀልዱት አንድ ቀልድ አለ ` አዝግሞ በገረድኮ፣ እስክትመጣ ሚስትኮ' የሚሉት።

ልጅ፣ አባቱን ለትምህርት ቤት አንድ የማቀርበው የቤት ስራ አለብኝ ብትረዳኝ ብሎ ይጠይቀዋል። አባትም በደስታ ልጄ ማለት!

ልጅ፣ ፖለቲካ ማለት ምን ማለት ነው?

አባት፣ ዌል! ቤታችንን እንደ ምሳሌ እንውሰድ። እኔ ለምሳሌ አባወራ እንደመሆኔ መጠን ሰርቼ የማመጣው የወር ደመወዝ አለ፤ እኔን እንደ ቶ፥ ብሌየር ብትወስደኝ እናትህን ደግሞ ገንዘቡን ተቀብላ ቤቱን ስለምታስተዳድር እንደ እንግሊዙ ገንዘብ ሚንስቴር ጎርደን ብራውን ቁጠራት፤የአንተን ፍላጎትህን ስለምናሙዋላልህ አንተን ህዝብ ብለን ልንጠራህ እንችላለን፤ የቤት ሰራተኞችንን ደግሞ የሰራተኛው መደብ ብለን ልንጠራት እንችላላን፤ ትንሹን ወንድምህን ደግሞ የወደፊቱ ተስፋ ስለሆነ የነገው አገር ተረካቢ አበባብለን ልንጠራው እንችላለን፣ አሁንገባህ ልጄ? ፖለቲካ ማለት እንደዚህ ነው፣ ይለዋል።

ልጅ፣ ርግጠኛ ሆኜ መናገር አልችልም ግን ያልከኝን እንዲገባኝ ለማድረግ እሞክራለሁ ብሎ ምሽቱን ከአባቱ ይለያያል።

በዚያ፥ እለት ሌሊት ታናሽ ወንድሙ ሽንትና የተፀዳዳው ነገር ስላልተቀየረለት እየቆጠቆጠው ምርር ብሎ ሲያለቅስ ታላቅ ወንድሙ ይነቃና እናትና አባቱን ለመቀሰቀስ ወደ መኝታ ቤት ሲገባ እናት ድብን ያለ እንቅልፍ ውስጥ ሆና መስማት እንደማትችል ያውቃል፣ አባት ደግሞ ከመኝታ ቤቱ ውስጥ የለም፤ ወደ ሰራተኛዋ መኝታ ቤት ሲሄድደግሞ በሩ ተዘግቶ ያገኛል፣ በቁልፍ ቀዳዳ ውስጥ አጮልጎ ሲመለከት ለካስ ወላጅ አባትከሰራተኛዋ ጋር ፊንጠዝያ ላይ ነው፣ ልጅ በመጣበት እግሩ ወደ መኝታ ክፍሉ በመመለስለሊቱን እንደምንም ብሎ ያነጋና ጠዋት ቁርስላይ፤ አባባ፣ አሁን ፖለቲካ ማለት ምን እንደሆነ በደንብ ገባኝ ይለዋል።አባትም፤ ` ጎበዝ ልጄ ባንተ ግንዛቤና በራስህ ቃል እስቲ ፖለቲካ ምን ማለት እንደሆነ ተንትነህ ንገረኝ' ይለዋል። ልጅም፤ ` ደህና አባባ! ቶ፥ ብሌር ሰራተኛውን መደብ በሚዘውርበት ጊዜ፤ ጎርደን ብራውን ደግሞ ድምፁን አጥፍቶ በተኛ ጊዜ፤ ህዝብ ደግሞ በአጠቃላይ የተገባለትን ቃልኪዳን ባልተፈፀመለት ጊዜ እና የወደፊቱም ተስፋ ደግሞ ጭራሽ ጨቅይቶ እንዲቀር በሚደረግበት ወቅት ፖለቲካ የሚለው ቃል ትርጉሙ ምን እንደሆነ አሁን ነው የገባኝ' በማለት ለአባቱ አጠይሞ ይነግረዋል።

ፖለቲካን እንደ ድርያ በአጠቃላይ ባንመለከተውም ፖለቲካ ውስጥ ገብተው ያለሙያቸውየሚዘባርቁትን ሰዎች ካየን ፖለቲካውን ከመዳራት አልፈው ሲያረክሱት በድፍን አፍሪቃችንእንመለከታለን። ሀገራችን ውስጥ በግንቦት 1983 የመጣው የወያኔ መንግስት ገና በትረ መንግስቱን ሲጨብጥ ህዝቡን ለማረጋጋትና ተቀባይነት ለማግኘት ያልገባው ቃል ኪዳንና ያላበላን የመና ተስፋ የለም፣ በቀን 3 ጊዜ እንድንበላ ከጠቅላይ ሚ፥ስትራችንየተገባልን ተስፋ እንደተጠበቀ ሆኖ።

በመከራ የፀናው ህዝባችን የጣር ወቅቱ በየጊዜው እየተጨመረለት ሸምቀቆው እየጠበቀበት በመዋቅር ማስተካከያ ሰበብ በብዙ ሺህ የሚቆጠረው ሰራተኛ መደብ ከስራው ላይ

እየተነቀለ፤ ያለ ጡረታና ያለበቂ ዋስትና እየተባረረ በአሁ፥ ወቅት ይገኛል።አባውራው ከስራው ላይ በሚነቀልበት ጊዜ ጣጣውን ይዞ የሚጉዋዘው እሱ ብቻ ሳይሆን በአንድ አባውራ በአማካኝ 8 ልጆች ጭምር እንደሚሆን አያጠራጥርም። ይህ የሰቆቃና የመከራ አስተናጋጅ መንግስት በህዝብስቃይ መደሰት የጀመረው የኢትዮጵያን መከላከያ ሰራዊትን፣ የህንፃ ኮንስትራክሽን መስሪያ ቤትን፣ የወባ ድርጅትንና ወዘተ በማፈራረስ ተለማምዶ ነው።

በእንባ የተደራጀው መንግስት ይሄው አሁን በአዲስ አበባ መስተዳድር ጀምሮ፤ በፖሊስ፣ በመምህራንና ወዘተ ውስጥ እንደሚቀጥል እየነገረን ነው። የሚገርመው አባራሪዎቹ፣ የአቅም ግንባታ ሚ፥ስትሩና በአጠቃላይ ነዳፊዎቹ 12ኛ ክፍልን ያልጨረሱና የኮሌጅ ትምህርታቸውን በተገቢው ሁኔታ ያላጠናቀቁ መሆናቸው ነው። ታዲያ እነሱ እከሌ12ኛ ክፍል አልጨረሰምና ዝቅ ብሎ መዝገብ ቤት አለያም ተንሳፋፊ ብሎ ለመወሰን የሞራሉ ብቃት አላቸው? ድፍን የአዲስ አበባን ሰራተኛ እንደ ማትሪክ ተፈታኝ ውጤትተጠባባቂ ሁልጊዜ ግርግዳ ላይ ስሜ ተለጥፎዋል አልተለጠፈም በሚል የሰቆቃ ህይወት የሰራኛውን ስነ ልብና ስነ አእምሮ መስለብ ይገባል???

መፍትሄው፣ ቁጭ በሉውን መንግስት በስራ ማቆም አድማና በመሳሰሉት ተቃውሞዎችአጥለቅልቆማንበርከክ እና ከስልጣን ማስወገድ ነው፤ እኔ ጋር አልደረሱምና አንገቴንቀብሬ አሳልፌ መኖር ይሻላል ብለን ከመረጥን ግን፣ የመከራው ቀን እየተራዘመ መሄዱየማይቀር ነው። የማይሰሩ ተረቶቻችንም መቀየር ያለባቸው ይመስለናል፤ ቀን እስኪያልፍበትግስት ማሳለፍ፣ የሚሉት አይነቶቹ!